**ፕሬስ ሪሊዝ**
**ታህሳስ 10 ቀን 2000 ዓ.ም**
**ማስታወቂያ ሚኒስቴር**

**በኦጋዴን ሽብርተኞችን በመደምሰስ እንቅስቃሴ ሕብረተሰቡ እያደረገ ካለው ሁለገብ ድጋፍ ውጭ ሲቪሎች በውጊያ ግምባር የተሳተፉበት ሁኔታ ፈጽሞ የለም**

ራሱን " የኦጋዴን ብሔራዊ ነፃነት ግንባር" (ኦብነግ) በማለት የሚጠራው አሸባሪ ቡድን ሲያካሂድ የቆየውን ፀረ ሰላም እንቅስቃሴና የሽብር ጥቃት ለማምከን የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት ከክልሉ መንግሥትና ከአካባቢው ሰላም ወዳድ ሕብረተሰብ ጋር በመሆን የተጠናከረ ሰፊ እንቅስቃሴ በማድረግ የአሸባሪው ቡደን በርካታ አባላትን ለመደምሰስና ለመማረክ እንዲሁም የቀረው ኃይሉም እንዲበታተን መደረጉ ይታወሳል፡፡ ይህ እርምጃም የፀረ-ሰላም ኃይሎች በተደራጀ መልኩ በአካባቢው በመንቀሳቀስ በሰላማዊ ዜጎች ሕይወትና በልማት ተቋማት ላይ የሽብር ጥቃት እንዳይፈጽሙ ያስቻለ ውጤት ማስገኘቱ ይታወቃል፡፡ ይህን ተከትሎም በነዚህ ፀረ-ሰላም ኃይሎች ምክንያት በአንዳንድ አካባቢዎች ተስተጓጉሎ የነበረውን የሰብዓዊ እርዳታና የልማት እንቅስቃሴ ለማስቀጠል ተችሏል፡፡ በቅርቡም የተመድ የሰብዓዊ እርዳታዎች ጉዳይ ኃላፊ የሆኑት ሚ/ር ጆን ሆልምስ አካባቢውን ጎብኝተው በሰጡት ማረጋገጫ ተስተጓጉሎ በቆየው የእርዳታ አቅርቦት ምክንያት የከፋ ሰብአዊ ቀውስ እንዳልደረሰና የእርዳታ ስርጭቱን ለማቀላጠፍ መንግሥት አግባብ ካላቸው የእርዳታ ደርጅቶች ጋር በቅርበት እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የአካባቢውን ሰላም በአስተማማኝ ከማስጠበቅና የልማት ፕሮጀክቶችንና ፕሮግራሞችን ቀጣይነት ከማረጋገጥ አኳያ ፀረ-ሰላም ኃይሎችን እግር በግር በመከታተል የመመንጠሩ ተግባር በክልሉ መንግሥትና በሕብረተሰቡ ሙሉ ተሳትፎ ተጠናክሮ ቀጥሎ ውጤታማ እየሆነ ይገኛል፡፡ በዚህ ረገድም በዋናነት ከክልሉ የተለያዩ ጎሳ አባላትና ኗሪዎች የተውጣጣ የአካባቢ ሚሊሺያ አባላት ከመከላከያ ሰራዊቱ ጋር በመቀናጀት ፀረ- ሰላም ኃይሎችን በማሳደድና በመደምሰስ ላይ ይገኛሉ፡፡

ይህ ባለበት ተጨባጭ ሁኔታ ዘጠኒውዮርክ ታይምስ እ.ኤ.አ ዲሴምበር 14ሐ2007 ባቀረበው ዘገባ የኢትዮጵያ መንግሥት ዶክተሮችን፣ መምህራንን፣ የቢሮ ሠራተኞችንና በተመድና በዓለም ባንክ ድጋፍ የሚካሄዱ የልማት ፕሮጀክቶች ተቀጣሪዎችን ጨምሮ ምንም ዓይነት ወታደራዊ ሥልጠና የሌላቸውን ሲቪሎች ፀረ-ሰላም የሆኑትን የኦብነግ ሽብርተኞችን እንዲዋጉ በግምባር አሰልፏል ሲል ሃሰተኛና መሰረተ ቢስ ዜና አሰራጭቷል፡፡

በመሰረቱ ከመከላከያ ሰራዊቱ ጎን በመሆን የፀረ ሰላም ኃይሎችን በመታገል ላይ ያለው መላው ሰላም ወዳድ የአጋዴን ሕዝብ ሲሆን በተለይም የአካባቢው ሚሊሻዎች በዚህ ረገድ ግምባር ቀደም ሚና ይዘው በመንሳቀስ ላይ እንደሆኑ በግልጽ ይታወቃል። የአካባቢ ሚሊሻዎች ከመደበኛ ሰራዊት አባላት የሚለዩት በግላቸው በመደበኛነት የራሳቸው የሆነ የመተዳደሪያ ሥ ራ ያላቸው ሆኖ የአካባቢአቸውን ሰላምና ደህንነት በጋራ ለመጠበቅ የሚያስችላቸው ሥልጠናና ትጥቅ ያላቸው መሆኑ ነው። የዚህ ዓይነት አደረጃጀት ያላቸው የአካባቢ ሚሊሻዎች በሁሉም የአገሪቱ ክልሎች በፈቃደኝነት ተመልምለውና ለአካባቢ ጥበቃ ብቁ የሚያደርጋቸው ወታደራዊ ስልጠና ወስደው የአካባቢያቸውን ሰላምና ደህንነት በማስጠበቅ ላይ ይገኛሉ። ይህ አይነት አሰራር በሃገሪቱ የቆዬና የዳበረ ጠቃሚ ልምድ እንደሆነ ይታወቃል።

ዘ ኒውዮርክ ታይምስ በተዛባ ሁኔታ እንዳቀረበው በአጋዴን አካባቢ ምንም ዓይነት ሥ ልጠና የሌላቸው ሲቪሎች በግዳጅ አብነግን በግንባር እንዲዋጉ የተደረገበት ሁኔታ ፈፅሞ የለም። መንግሥት የሽብርተኛውን ቡድን ኃይሎች በግምባር እየተፋለመ ያለው በዋናነት ወታደራዊ ሥልጠና ባላቸውና በታጠቁ የአካባቢው ሚሊሽያ አባላትና በመከላከያ ሰራዊቱ ግምባር ቀደም ድጋፍ እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል። ይህ እየተደረገ ያለውም የሰላማዊ ሲቪሎችን ደህንነትና የአካባቢውን ሰላም ለማስጠበቅ ሆኖ ሳለ የሽብርተኞች አንዱ ዒላማ የሆኑትን ሲቪሎች አደጋ ላይ የሚጥል እርምጃ መንግሥት የሚወስድበት ሁኔታ ፈጽሞ ሊኖር አይችልም። በእርግጥ ሲቪሉ ህብረተሰብ ሽብርተኞችን በመጠቆምና በማስያዝ፣ ለሚሊሻውና ለመከላኪያ ኃይሉ አቅጣጫ በማመላከትና በመንከባበከብ የበኩሉን ከፍተኛ አስተዋጽኦ በሁለንተናዊ መልኩ እያደረገ ይገኛል።

ይህ የሕብረተሰቡ ተሳትፎ የሚበረታታና የሚደገፍ በመሆኑ ወደፊትም ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል። በዚህ ረገድ ሕብረተሰቡ በራሱና በጎሳ መሪዎች አስተባባሪነት እያደረገ ያለውን የራሱን ሰላምና ደህንነት የማስጠበቅ እንቅስቃሴ በማዛባት ዘ ኒውዮርክ ታይምስ ላይ የቀረበው ዘገባ ፈጽሞ የተሳሳተ፣ ተአማኒነት የሌለውና የአካባቢውን ተጨባጭና ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘበ በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል።